# ስለ ራኔት ኢትዮጵያ መግቢያ

ራኔት ማለት ከእንግሊዘኛዎቹ "RAdio" እና "InterNET" ቃላት፤ የተሰመረባቸውን ፊደላት በማገጣጠም የተገኘ ቃል ነው። የራኔት ዋናኛ አላማም የወርልድ ስፔስ ዲጂታል ሬዲዮንና የኢንተርኔትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጣመሮ በመጠቀም ሚቲዎሮሎጂ ነክ የሆነ ኢንፎርሜሽንን ከከተማ ርቆ በገጠር ለሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል የሚደርስበትን መንገድ ማመቻቸት ነው።

በራኔት ስርዐት ውስጥ የሚቲዎሮሎጂ ተቋማት በገጠር የሚኖረውን የህብረተሰብ ክፍል ይጠቅማሉ ብለው የሚያስቧቸውን የኢንፎርሜሽን አይነቶች በመለየት ወደ ኢንተርኔት ስርዐት ውስጥ እንዲገቡ (Upload) ያደርጋሉ። በሌላው ጫፍ ያሉና በገጠር የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች እነዚህን መረጃዎች አግኝተው ለመጠቀም የሚያስፈልጋቸው የወርልድ ስፔስ ዲጂታል ሬዴዮኖች እና በዊንዶውስ ኦፐሬቲንግ ሲስተም የሚሰራ ኮምፒውተር ብቻ ነው። ይህ ማለት ደግሞ የስልክ መስመር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ከሚሰጡ ተቋማት ጋር መዋዋል ሳያስፈልጋቸው ሬዲዮኑንና ኮምፒውተሩን በማገናኘት ብቻ መረጃዎ-ቹን ወደ ኮምፒውተሩ እንዲገለበጥ (download) በማድረግ በመረጃዎቹ መጠቀም ይችላሉ።

በዚሁ መሰረት የራኔት ኢትዮጵያ አስተባባሪዎችም በገጠሩ የሀገራችን ክፍል የሚኖረውን የህብረተሰብ ክፍል ይጠቅማሉ ብለው ያሰቧቸውን ሚቲዎሮሎጂ ነክ መረጃዎች በዚህ ድረ-ገፅ ላይ እንዲቀመጡ ያደርጋሉ። የወርልድ ሰፔስ ዲጂታል ሬዲዮ እና በዊንዶውስ ኦፐሬቲንግ ሲስተም የሚሰራ ሬዲዮ ያላቸው የገጠር ልማት ሰራተኞች፣ የአርሶ አደር ህብረት ስራ ማህበራት ወይም የገጠሩን ማህበረሰብ በልዩ ልዩ መንገድ የሚያግዙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በዲጂታል ሬዲዮው አማካይነት ወደ ኮምፒውተሩ የተገለበጠውን መረጃ በገጠር ለሚኖረው የህብረተሰብ ክፍል አንዲዳረስ ማድረግ ይችላሉ።

ሕብረተሰቡም እነዚህን መረጃዎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው በመጠቀም እራሱንና ንብረቱን ከሚቲዎሮሎጂ ነክ አደጋዎች በመጠበቅ እና ምርታማነቱም እንዲጨምር በማድረግ ረገድ፤ ራኔት ኢትዮጵያ ሀገራችን ለተያያዘችው የድህነት ቅነሳ እንቅስቃሴ የበኩሉን ድርሻ እንደሚያበረክት ይታመናል።

ከዚህ አንፃር በገጠር የሚኖረው ወገናችን በራኔት ስርዐት በሚገባ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ አቅም ያላቸው ተቋማት የወርልድ ሰፔስ ዲጂታል ሬዲዮኖችን፣ ኮምፒውተሮችን እንዲሁም ሌሎች አጋዥ ቁሳቁሶችን ገዝተው በየገጠሩ ለሚገኙ አማካይ የመረጃ ማሰባሰቢያ ማዕከላት እንዲሰጡ ይበረታታሉ። ከዚህ በተጨማሪም ለህብረተሰቡ ይጠቀማሉ ብለው የሚያስቧቸውን ሚቲዎሮሎጂ ነክ የመረጃ አይነቶችን ለይተው እንዲጠቁሙን እያበረታታን፣ ራኔትን በተመለከተ ሊያገኙን ለሚፈለጉ ሁሉ ዋናው ገፅ ላይ ያለውን አድራሻ መጠቀም እንደሚችሉ በደስታ እንገልጻለን።